# የዳግማዊ አጼ ቴዎድሮስ የሕይወታቸው መጨረሻ ሰዓት እና የመቅደላ ዝርፊያ

**በስፍራው በአካል በመገኘት የአሜሪካን ጋዜጠኛ /ደራሲ እንደመዘገበው**

**ትርጉም በቆንጂት መሸሻ**



ሁለት የእንግሊዝ ወታደሮች: ከሳር ድርቆሽ ክምር አጠገብ አንድ ሽጉጥ የጨበጠ ሰው ይመለከታሉ :: ሊተኩሱ ሲደቅኑበት በአያቸውም ጊዜ ከክምሩ በስተጀርባ ይሰወራል: ቀጥሎም በእርግጥ ተኩስ ይሰማሉ:: ተኩስ ከሰሙበት ቦታ ሲደርሱ ከሳሩ ድርቆሽ ክምችት አጠገብ ያዩት ሰው መሬት ላይ ወድቆ: ተዘርግቶ በቀኝ እጁ ሽጉጡን እንደጨበጠ ነፍስ ውጭ ነፍስ ግቢ ላይ ሆኖ ያገኙታል::

ሽጉጡ ሰደፍ ላይ በብር የተለበደ ጽሁፍ እንዲህ ይላል:-

**ከታላቋ ብሪታንያ እና አየርላንድ ንግሥት**
**ንግሥት ቪክቶሪያ**

**ለአገልጋዩ ፕላውዴን ለለገሱት ርህራሄ**
**ምስጋና ይሆን ዘንድ ይህችን ትንሽ መታሰቢያ**

**ለቴዎድሮስ**
**የአቢስኒያ ንጉሠ ነገሥት**
**ተበረከተ**
1854

ይህ ፍንትው ብሎ የተገለጸ ታሪክ በ1874 ዓ.ም ሄንሪ ኤም. እስታንሊ የተባለው የኒውዮርክ ሄራልድ ጋዜጣ ተቀጣሪ እንደ አውሮፖ አቆጣጠር በ1868 በክቡር ጄኔራል ሮበርት ናፒዬር የተመራው የእንግሊዝ ጦር ጋር ወደ ኢትዮጵያ በምጓዝ "ኮማሲ እና መቅደላ" በተሰኘው የሚመስጥ መጽሐፉ የመዘገበው ነው:: ይህ አጭር ጽሑፍም የተጻፈው የንጉሡን ሕይወት ማለፍ ተከትሎ እስታንሊ በገጽ 449-464 ያሰፈረውን ሀተታ ማስረጃ መሰረት በማድረግ ነው::በተጨማሪም በእውን ያያቸውን ከመቅደላ የተዘረፉትን ቅርሶች ገጽ 454-462 በዝርዝር ያስቀምጣል:: የእንግሊዝ ጦር ወደ ኢትዮጵያ የዘመተበት ምክንያት ንጉሡ ለንግሥት ቪክቶሪያ የሁለቱ ሐገራት ወዳጅነት መመሰረት እና ማጠናከር በተመለከተ ለጻፉላቸው ደብዳቤ መልስ ስለተነፈጋቸው: በአጠፋው ያሰሯቸውን የእንግሊዝ መልክተኞች ከእስር ለማስፈታት መሆኑ ሊታወስ ይገባል::

ጸሐፊው እስታንሊ በመቀጠል እንዲህ ይተቻል:-

የአጼ ቴዎድሮስ ሬሳ የእንግሊዝ ጦር ከቆመበት መሀከለኛ ስፍራ ተወስዶ ነበር:: በሰአቱ የእንግሊዝ ሰራዊት መቅደላን በሙሉ ተቆጣጥረው በደስታ "ንግሥታችን ትባረክ" እያሉ ሲደነፉ እና በደስታ ሲጮሁ ይሰማ ነበር::

በዚህ ሰዓት ንጉሡ ክፉኛ ቆስለው በማጣጣር ላይ ቢሆኑም ሕይወታቸው አላለፈም ነበር:: ይህን የተመለከቱ የሐገሩ ሰዎች ስማቸውን እየጠሩ ሲጮሁ ማንነታቸው ተገለጸ::
ጸሐፊው ሲቀጥልም በድኑን በዚህ ዓይነት ይገልጻል: ...." የሐገሩ ተወላጅ: ስውነቱ በረሃብ የተዳከመ: ከወገቡ በላይ መናኛ ያገለገለ የተቀደደ እጀጠባብ የለበሰ: ከውስጥ ደግሞ አዳዲስ ልብስ ::" በዒላማ ተኳሽ እንዳይመታም ተራ ሰው በመምሰል ሲዋጋ የነበር::

መልኩ ጠይም: ከንፈሮቹ ቀጠን ጠበብ ያሉ: ጥርሶቹ በጣም የነጡ ናቸው:: ስልክክ ያለ አፍንጫውም ትንፋሽ እየከዳችው መሆኑ ይታያል:: ፊቱ ሰፋ ያለ: ጉንጭ እና ግንባሩ የጎላ: ቅንድቡ የተሚላ ነው::ጸጉሩም ለሦስት ተከፍሎ ከፊት ወደ ኋላ ሹርባ ተሠርቶአል:
ሰውነቱም ደረተ ስፊ እና ጡንቻማ ሲሆን የበድኑ ቁመቱም "5ፊት 8 ኢንች" (1.8 ሜትር) ይሆናል::"

ወዲያው በተደረገው የሬሳ ምርመራ: "ቀኝ እግራቸው ቀላል ቁስል ሲታይበት በአፍ ወደ ውስጥ የተተኮሰው ጥይት ግን የውስጥ አፋቸውን አቃጥሎ: ላንቃቸውን አውድሞ: ማጅራታቸውን በስቶ እንደገደላቸው ታወቀ::" በዚህም ሕይወታቸው ያለፈው ጥይት በመጠጣት መሆኑ ተረጋገጠ::"

የንጉሥ ቴዎድሮስ በድን መሆኑ ከተርጋገጠ በኋላ:..
"የአየርላንድ ወታደሮች እግራቸውን በመያዝ እያንገላቱ ጎትተው ወደ ድንኳኑ ወሰዱት: በዚያ የመጨረሻ ትንፋሻቸውን ተነፈሱ::"

በቦታው የነበሩት የእንግሊዝ ወታደሮችም ያላግጡባቸው ነበር:: "ነገር ግን ከማህላቸው አንዱ እርቃናቸውን ሸፍኖ: ክንዳቸውን አጥፎ: እጃቸውን ደረታቸው ላይ አሳረፈ:" ወዲያውም ለማየት የተሰበሰበው ሰው ብዛት እየጨመረ ሔደ "ከሰዎቹ ማህልም የቀድሞ እስረኞቹ ተመልክተው ማንነታቸውን አረጋገጡ::

ሰር ናፒዬር በፈረስ ተቀምጠው ሬሳውን ለማየት መጡ:ተመለከቱ:: ምንም ዓይነት የርህራሄ ቃል አልተናገሩም::

ጸሐፊው ሲቀጥልም: " እኔም በሸራ ቃሬዛ ላይ ያረፈው የመቅደላው ጌታ ሬሳ ወደአለበት ስፍራ በዝግታ ተራመድኩ:: ቅጥ ያጣ የወታደር ስብስብ እና ሌሎችም ሰዎች እርስ በእርስ እየተጋፉ በደም የተለወሰውን የቴዎድሮስ እጀ ጠባብ ቁራጭ ጨርቅ ለመውስድ ሲታገሉ አየሁ:: እርቃኑን እስኪቀር ድረስ ለሬሳው ጠባቂ አልተደረገለትም:: በቃሬዛው እንደተንጋለለ የአእምሮ ደካሞችእና ባለጌዎች መዘበቻ መቀለጃ ተደረገ:" ጉዳዩን ሰር ናፒዬር እንደሰሙ ሬሳው እንዲለብስ እና ለማግስቱ ፍትሃት እንዲሁም ቀብር እንዲዘጋጅ አዘዙ:: ንግሥቲቱ በጠየቁት መሰረት በማግስቱ ሬሳው በግል ቄሳቸው ተፈትቶ በመቅደላ የሚገኝ ቤተክርስቲያን ተቀበረ::

የአጼ ቴዎድሮስ የሕይወታቸው የመጨረሻ ዕለት April 12 1868 እኩለ ሌሊት ላይ የእንግሊዝ ጦር መሪ ጀኔራል ናፕዬር በማግስቱ ቀን April,13 ከጠዋቱ ሦስት ሰዓት እጅ ካልሰጡ ጦሩ እንደሚወጋቸው የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ ሲደርሳቸው ይጀምራል::

April 13 ቀን ጠዋት ቦግ ያለ ፀሀይ: ረፈድ ሲል ከባድ ዝናብና መብረቅ: ቀጥሎ ደግሞ ፀሀይ ስትጠልቅ ድንቅ ውበት የታየበት ቀን ነበር::

የእንግሊዙ ጦር አዝማች ንጉሡ እጅ እንዳልሰጡ እና ወደ ጎጃም ምድር አምልጠዋል የሚል የተሳሳተ መረጃ በመቀበላቸው የተነሳ ንጉሡን በሕይወት ወይንም በድናቸውን ይዞ ለሚያስረክብ የ50,000 ዶላር ሽልማት እንደሚያደርጉ መልእክት አስተላለፉ:: ንጉሡ በመቅደላ ጀርባ እንዳያመልጡ ጥንቃቄ በማድረግ ሦስተኛ ድራጎን ብርጌድ የተባለውን "እንደ አጥር አሰለፉት":: በዚህ ዕለት April, 13 የእንግሊዝ ጦር ሙሉ በሙሉ ለጦርነት ዝግጁ ነበር:: ጦሩ 1,600 ኢውሮፓውያን: 800 ቤሉቺስ: 800 ፑንጃቢስ: 42 ዝሆኖች: ሌሎችም ጭነት ተሸካሚ እንስሳት የተካተቱበት ነበር::

አዳዲስ መሳሪያ የታጠቀው የእንግሊዝ ጦር በፍጥነት ገስግሶ የሥላሴን የፋላን ኮረብታዎች ተቆጣጥሮ ከቀኑ ስምንት ሰአት መቅደላ ምሽግ በር ደረሰ:: የመቅደላ መግቢያ በርን በሜዳ መድፍ ደበደቡት:: ጸሐፊው እስታንሊ እንደጻፈው:- በዚህ ሰዓት ቴዎድሮስ በነጭ ፈረስ ተቀምጦ እየተዟዟረ የጠላትን ግስጋሴ እየተመለከተ የተመናመነ ጦሩን በጀግነት እንዲዋጋ ያበረታታ ነበር ይለናል:: ንጉሡ ከፍ ባለ ድምፅ ሰራዊቱን "ግፉ ተዋጉ! ሴት ይመስል እነዚህን ጥቂት ጦረኞች ለማጥቃት ፈራችሁ?" ይሉ ነበር:: ይሁን እንጂ ከቅርብ የሚተኮሰው የመድፍ ብረት ኳስ ተዋጊውን ስለበተነው በአስችኳይ ወደኋላ እንዲያፈገፍጉ ተገደዱ:: ሆኖም ከጥቂት ታማኞች ጋር ሆነው የመቅደላን ምሽግ ሰብሮ እስከገባበት የመጨረሻው ስዓት ድረስ የጠላትን ጦር ገጠሙት::

አጼ ቴዎድሮስ ባለአንጣዎቻቸው ላይ ይፈጽሙት የነበረ የጭካኔ ድርጊትን ለማሳየት በሚመስል አጻጻፍ: እስታንሊ በApril 9 ቀን 309 የተቀናቃኝ ሰዎችን ሬሳ ተመለከትሁኝ በማለት ይመሰክራል::

ከንጉሡ አሳዛኝ ሞት ቀጥሎ ዲሲፒሊን የነበረው የእንግሊዝ ጦር መረን ለቆ "ልዩ ልዩ የወታደር ቡድኖች " በመፍጠር ተሰለፈ:: እነእዚህ ለዝርፊያ የወገኑ ወታደር ቡድኖች በመላው መቅደላ አምባ ተሰራጩ:: የንጉሡን እቃ ቤት ግልብጥብጡን አወጥተው በዘበዙት: ወደ ንጉሡ መኖሪያ ቅጥር ግቢ ገብተው "የፈለጉትን ሲያነሱ ሲመለከቱ: ኪሳቸው ሲከቱ: ያልፈለጉትን ሲወረውሩ በመከታተል ዘረፉት::"

እንደገለጻው የመቅደላ አምባ ላይ አልፎ አልፎ የሚታዩ ብዙ ልዩ ልዩ ዓይነት መኖሪያዎች ነበሩ:: በሀር ወይንም በሸራ የተሠሩ ድንኳኖች: ጎጆዎች: ዛኒጋባዎች እና የመንገድ አልጋዎች ሌሎችም ነበሩ: "እያአንዳንዱን መኖሪያ የከበበው ዘራፊ ቡድን ዓይናቸው ያየውን እቃ ሁሉ ሲመረምሩ ሲወያዩ ሲያነሱ የመሰላቸውን ኪሳቸው ሲያስገቡ: ሌላውን ደግሞ እንደአሰኛቸው ሲጥሉ:ሲቀዱ :ሲያወድሙ ይታያሉ::" በዚያ የሚሆነውን ሲደመድምም:-....ልዩ ሆነው በተተከሉ ቋሚ ድንኳን ቤቶች ታላቅ ስብስብ ነበር:: በእነዚህ የቅርስ ክምችት በያዙ ድንኳኖች ዙሪያ ታላቅ ረብሻ ግርግር ነግሿል:: በስፍራው ያየውን ሲያጋልጥ:...ከዘራፊ ወታደሮች ጎን ሦስት ስግብግብ ሚሽነሪዎች: እንዲሁም ትውልዳቸው አንዱ ከፕረሽያ ሁለተኛው ከጀርመን ሦስተኛው ከሩስያ የሆነ መካኒኮች አስቀድመው በስፍራው በመድረስ ቅርሱን ተከፋፍለው ይዘውት ነበር.. ይላል::

በጠቅላላው ከመቅደላ የተዘረፈውን ቅርስ እንደሚከተለው ይተነትናል:-

እስታንሊ ዝርዝሩን ከማቅረቡ በፊት እንዲህ ይተቻል:: "በየቦታው ወድቆ ያለውን እቃ አንድ አስረኛውን እንኳ ለመዘርዘር አድካሚ እና ፍሬ ቢስ ነው:" ሆኖም ከፊቱ የተነጠፈው የቅርስ ክምችት መሀል ዋና ዋና የመሰሉትን ለይቶ ይጠቅሳል::

" አንደኛው ድንኳን ውስጥ በአማረ ቀለማም ክሮች የተሰራ የኢትዮጵያ መንግሥት መታወቃያ የሆነው የይሁዳ አንበሳ ምስል:...ሌላው ውስጥ እንዲሁ የአንበሳ ምስል የተቀረፀበት የንጉሡ ማህተም ተገኘ:: ከንፁህ ወርቅ የተሰራ ፅዋ በሚስተር ሆልምስ እጅ ገባ:: ፅዋዉ ላይ የሚከተለው ጽሁፍ በጥንቱ የኢትዮድያ ቋንቋ ተቀርፆበታል::

**ዳግማዊ ኢያሱ እና ሚስቱ ወለተ ጊዮርጊስ**

**ቅድስት ቁስቋም የሥጋ እና የነፍስ**

**መድሃኒት ትሆናቸው ዘንድ**

**ይህን ፅዋ አበርክተዋል**

በ15ተኛው መቶ ክፍለ ዘመን

ሦስት መቶ ዓመት እድሜ ያካበተው ከንፁህ ወርቅ የተሰራ ምንአልባትም ክብደቱ ከስድስት ወይንም ሰባት ትሮይ አወንስ የማያንስ የአቡኑ አርዌ ብርት:.. አራት የነገሥታቱ ዘውዶች ከእነዚህም መሀል ሁለቱ በረቂቅ የፊሊግሪ ጥበብ የተሠሩ ከፍተኛ ገንዘብ የሚያስገኙ እና በእንግሊዝ ሙዝየም ሊቀመጡ የበቁ...ከሚያማምሩ እቃዎች መሀከል ከአውሮፖ መንግሥታት የተጻፉ በቆንጆ ማህደር የተሸፈኑ ደብዳቤዎችን: የሀገር ውስጥ መረጃ ወረቀቶችን የያዘች አነስ ያለች በፐርል ዶቃ ያጌጠች የቢሮ ጠረጴዛ ..ለመቁጠር የሚከብድ ከወርቅ: ከብር: ከነሀስ የተስሩ ቆንጆ መስቀሎች: ፅናዎች:...የወርቅ የብር ምግብ ማቅረቢያዎች: ማንቆርቆሪያዎች:ሳህኖች: ድስቶች: አያሌ ትልቅ ትንሽ ፍንጃሎች: በወርቅ በብር ያጌጡ ዋንጫዎች:....ቦሂሚያን ብርጭቆዎች: ሴቨር ቻይና: የእስታፈርድሻየር ሸክላ ሳህኖች: የሻምፔን (ፈርንሳይ) ወይን ጠጅ:.... የግሪክ የስፔን የእየሩሳሌም ወይንጠጅ :በርጋንዲ:.. የዮርዳኖስ ወንዝ ውሀ: .. አረቄ እና ጠጅ በገምቦ:...ሳጥን ሙሉ ልዩ ልዩ ዓይነት እቃዎች: እንዲሁም ጽጌ ረዳ: ነጭ: እና ሌሎች ቀለሞች የሆኑ የሀር ድንኳኖች:....የፐርዢያ የኡሻክ ብሮሳ ኪድሚንስትር የሊዮንስ አበባ ምንጣሮች:... የጎፈር ካባዎች: የአንበሳ ጋማ ለምድ: የነብር የቀበሮ ቆዳዎች:...ግሩም ሆነው የተሰሩ በወርቅ በብር ያሸበረቁ ኮርቻዎች:... በብር የተለበዱ በጣም ብዙ ጋሻዎች:...ጎንደርና ጎጃም ያፈራቸው የተዋቡ የክብር ጃንጥላዎች:... ሰይፎች: ሾተሎች: ጎራዴዎች እንዲሁም በሁለት በኩል ስለት ያላቸው የስኮትላንድ ጎራዴዎች: ቢላዎች: አያሌ የእግር የእጅ ብረቶች:..

ከፐርዢያ: ከደማስከስ: ከህንድ: ሀገራት የመጡ በጥልፍ ያጌጡ በወርቅ የተለበዱ ቀለማቸው የሚያበራ የጨርቅ የቆዳ ማህደር የለበሱ ጩቤዎች: በሚያንጸባርቅ ቀለም የተሳሉ ስዕሎች የሚታይበት የብራና ቁልል:... መጽሐፍ ቅዱስ: የቅዳሴ የፀሎት መጻህፍት ክምር:...ለቁጥር የሚከብድ አልበሞች: የእንግሊዝ የአሜሪካ የፈረንሳይ የጣሊያን ምድረ መሬት ፎቶግራፎች ግማሾቹ መስተዋት ላይ የተነደፉ:...ጥበብኛ የቀረጻቸው ቢሮዎች ወንበር ጠረጴዛዎች::"

ጸሐፊው ያየውን እቃዎች በዝርዝር ካስቀመጠ በኋላ በዚያ አምባ ላይ የተሰራጨው ሀብት እና ቅርስ የነበረውን ሽብር እና ግርግር ምን ያክል እንደነበር ሲተች.... " ይህ ነው ብሎ ለመገመት በሚያዳግት ሁኔታ ጠቅላላው የመቅደላ አምባ ዳር እስከ ዳር ድረስ: ዳገቱን ጨምሮ : ከዚያም ሁለት ማይል (3.2 ኪሎ ሜትር) ርቀት አልፎ እስከ ካምፕ ድረስ በሺ የሚቆጠሩ እቃዎች ወድቀው ተዝረክርከው ይታይ ነበር::"

የሀራጅ ሽያጭ ከመጀመሩ አስቀድሞ እያንዳንዱ መኮንን ለሚመራው ጦር ተስማሚ የመሰለውን መታሰቢያ እቃ መረጠ::

በሦስተኛው ቀን ማለዳ ጠዋት የተዘረፈው ሀብት ተዘጋጅቶ ለሀራጅ ሽያጭ ቀረበ:: የእቃው ክምችት ግማሽ ኤከር (4,047 ካሬ ሜትር) ስፋት ያለውን መሬት ሸፍኖታል:: በዚያ የተገኙት ስም ዝርዝር ... ሚስተር ሆልምስ: የእንግሊዝ ሚዩዚየም ወኪል:..ኮለኔል ፍሬዘርር : የኃብታም ጦር መሪዎች ክበብ ሀብት ገገር: ሰብሳቢ: እንዲሁም ለጨረታ ተሰናድተው የመጡ ኃብታም ግለ ሰቦች ነበሩ:: በጊዜው የነበረውን የሞቀ ጨረታ ለአንባቢው በሚገልጹ ቃላት የእስታንሊ ጽሑፉን እንዲህ ይቀጥላል....
በአበጠ ኪሱ የተመካው ሚስተር ሆልምስ ዋና ዋና በተባሉት ቅርሶች የጨረታው አሸናፊ ነበር::
የቴዎድሮስ የልጅነታቸው ጋሻ ለሽያጭ ሲቀርብ: ውድድሩ ጋለ:: በአስር ዶላር የጀመረው ጨረታ ከሞቀ ውድድር በኋላ ኮሌኔል ፍሬዝርር በ200 ዶላር ገዛው::"
የሀራጅ ሽያጩ በሁለት ቀናት ተጠናቀቀ:: የተሰበሰበውም ገንዘብ ለተራ ወታደሩ ተከፋፈለ::

ሽያጩ ከተፈጸመ በኋላ እቃውን ከኢትዮጵያ ለማውጣት በሚያመች ዘዴ በ15 ዝሆኖች: 200 በቅሎዎች ጀርባ ተጭኖ ለረጅሙ ጉዞ ተደራጀ::

መቅደላ በእንግሊዞች እጅ በገባች በአራተኛው ቀን: 30,000 ኢትዮጵያውያን የመቅደላን አምባ ለቀው ወደ አምባላጌ ወረዱ:: የዚያኑ ዕለት ከሰዓት በኋላ: ተመልካቾች አንድ ሺህ ያርድ (915 ሜትር) ርቀት ያለው የሥላሴ ኮረብታ በስተደቡብ ዳገት ጥግ ጥጉን ይዘው ሲጠብቁ: የእንግሊዝ መንግሥት ኤንጅነሮች የመቅደላን አምባ እሳት ለኮሱበት አወደሙት:: እሳቱም በንፋስ ስለተዛመተ 3,000 ቤቶች ከነንብረታቸው ተቃጠሉ ተደመሰሱ:: እስታንሊ ዘገባውን በመቀጠል....."በባለሙያዎች ወደ እሳቱ የተወረወረው: ጥይት የጎረሰ ሽጉጥ: ጠመንጃ እና ቀለህ: እንዲሁም ተወንጫፊ የጦር መሳሪያ ባስነሳው ኃይለኛ ሙቀት ምክንያት ከፍንዳታው እየተስፈነጠረ የሚበረው ቁርጥራጭ ብረት እያፏጨ በአጠገባችን ያልፋል: ድምፁም ጆሮ ይደፍን ነበር:: አንድም ጎጆ ከእሳቱ ማእበል አላመለጠም::" ይላል::

የእንግሊዝ ጦር መቅደላን በእሳት ማእበል ከደመሰሰ በኋላ የዘረፈውን ሀብት ጭኖ ወደ ጠረፍ ጉዞ ጀመረ:: የሠራዊቱ 6,000 አባላት የኋላ ጦር: "ዳገቱን ወርደው ብቅ ሲሉ ከፍ ባለ ድምፅ መዝሙር እና ፉከራ ያሰሙ ነበር::"

ከመቅደላ የተዘረፈውን ንብረት ለማስመለስ በኢትዮጵያዊያን እና ሌሎችም ሃቀኛ ታሪክ ተመራማሪዎች የሚደረገው ጥረት ዘመን ተራማጅ ዘመቻ ሆኗል:: የተጋዘውን ታሪካዊ ጽሑፎች እና መጻህፍት: እንዲሁም የአጼ ቴዎድሮስ የግል ንብረቶች ስናስብ በጊዜው በዶክተር ሪቻርድ ፓንከርስት መሪነት የተካሔደው የንብረት ማስመለስ ትግል ድጋፍ የሚገባው ነው:: አ.ፍ.ሮ.ሜ.ት የተባለው ይህ ድርጅት በኢትዮጵያ እና በታላቋ ብሪታንያ ቅርንጫፍ የመሰረተ ሲሆን ባደረገውም ትግል የአጼ ቴዎድሮስን የአንገት ክታብ አስመልሶ ለኢትዮጵያ ታሪክ ጥናት ኢንስቲቲዩት አስረክቧል: በተጨማሪም ለንጉሡ ሐውልት እንዲቆምላቸው እየሠሩ ነው:: የእስኮትላንድ ተወላጅ የሆኑት ሬቨራንድ ማክሉኪይ በተባሉት በኤደንበሮ የቅዱስ ዮሐንስ ኤፒስኮፖል ቤተክርስቲያን ኃላፊ በጎ ሥራ: የቅዱስ ሚካኤል ፅላት በ February 2002 ወደ ኢትዮጵያ ተመልሷል:: ተመሳሳይ ጥረት እና ማስተዋል የሚጠይቅ ሌላ ጉዳይ: በእየሩሳሌም የሚገኘው የኢትዮጵያ ንብረቶች ሁኔታ ነው:: በኢየሩሳሌም ብቻ ሳይሆን: በጄሪኮ: እንዲሁም በሌሎች የእስራኤል ከተሞች የሚገኙ ታሪካዊ ይዞታዎች ሁሉ ሊጠበቁ ይገባል::

የአርቆ አስተዋዩ አወዛጋቢው እና አነጋጋሪው አጼ ቴዎድሮስ ሕይወት በዚህ ሁኔታ ተፈጸመ::
ጸሐፊው የሕይወታቸው መጨረሻ ቀን የሆነውን ሁሉ በሚመስጠው ጽህፉ ቁልጭ አድርጎ አስቀምጦታል:: የመጽሐፉ ዋና ዓላማ የእንግሊዝ ጦማበኢትዮጵያ ያገኘውን ድል መተንተን እንዲሁም 61 እስረኞችን ከ187 አሽከሮቻቸው 323 እንስሳትን ጨምሮ ከእስር ማስፈታት መቻላቸውን ማስረዳት ነው::ሆኖም የእስታንሊ ሥራ ታላቅ ድክመት የእንግሊዞች ድል የተገኘው በጊዜው ንጉሡ በጭካኔአቸው ምክንያት ብዙ የህዝብ ደጋፍ

እንዳልነበራቸው እና ተፎካካሪዎቻቸው መሪዎችም በግል ሥልጣን ማስፋፋት ተጠምደው እንደነበር አለመግለጹ ነው:: የእንግሊዝን ጦር የመቅደላ ጉዞ እንዲሳካ ምግብ በማቅረብ መንገድ በመምራት ከረዱት ከ"ልዑል ካሣ" በኋላም ከአጼ ዮሐንስ በስተቀር እስታንሊ ስለ ኢትዮጵያዊያን ያለው አስተሳሰብ የተቀዛቀዘ ይመስላል:: ይሁን እንጂ ጄነራል ናፒዬር ከአካባቢው ባለስልጣናት ጋር ከጠረፍ እስከ መቅደላ አምባ ድረስ ጦሩ ያለአንዳች እንቅፋት እንዲጓዝ የተሳካ ድርድር ማድረጉን ያስረዳናል::

አንደነቷን የጠበቀች እና በእስራኤል ያላትን ንብረቶች በተለይም የደር ሡልጣን ገዳምን የምታስከብር ጠንካራ ኢትዮጵያን ማየት የቴዎድሮስ ራዕይ እንደነኛር ሁሉ የትናንት የዛሬም ትውልድ ሁሉ ምኞት ሆኖ ቀጥሎአል::

---

1. ፅዋው ላይ የተቀረጸውን ጽሑፍ በተመለከተ...ትክክለኛውን የግዕዝ ጽሑፍ ከተክለ ጻድቅ መኩሪያ "ቴዎድሮስ እና የኢትዮድያ አንድነት 1981 ዓ.ም.) በተሰኘው መጻሐፍ ገጽ 446 ያገኘሁትን ወደ አማርኛ በማስተርጎም እዚህ አስገብቼዋለሁ::
2. የጦርነቱ ዘመን በእስታንሊ ጽሁፍ እንደሰፈረው በኢሮፓውያን አቆጣጣር ነው:: ለአንባቢ እንዲመች በማለት በቅንፍ የተቀመጡ ተጨማሪ ማብራሪያም ይገኝበታል::
3. ይህ ጽሑፍ ወደ አማርኛ የተተርጎመው በኪዳኔ ዓለምአየሁ እና ቆንጂት መሸሻ “THE LAST DAY OF EMPEROR TEWDROS II’s LIFE AND THE LOOT OF MAGDALA” ቢሚል አርእስት በ2011 በበየነ መረብ ላይ ከሰፈረው ጽሑፍ ነው::